# በኢትዮጵያ ሁሉንም የገጠር ተጠቃሚዎች አካል ጉዳተኞችን በተለይ ያካተተ የንፁህ መጠጥ ውሀ፤የአጠቃላይ ስነ-ንፅህና እና የግል ንፅህና መመሪያ



## ማህበረሰብ መር የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፤ የአካባቢና የግል ንጽህና (ኮዋሽ) መመሪያ

መጋቢት 2010 ዓ.ም.

**ማውጫ**

1. አካታችና ለሁሉም ተደራሽ ውሃ፣ የአካባቢና የግል ንጽህና ....................3
2. አካል ጉዳተኝነት ምን ማለት ነው? ....................4
3. በንጹህ ውሀ የአካባቢ እና የግል ንጽህና ፕሮጀክቶች እቅድ ዝግጅት፣ አስተዳደር፣ ኦፕሬሽንአገልግሎት አሰጣጥና ጥገና ላይ ሁሉአቀፍ ተሳትፎ፣ አስተዋጽኦና አካታችነት ....................10
4. የማህበረሰብ ዉሀ አቅርቦትና ስለ-ንጽህና አካታች መፍትሔዎች ....................12
5. አካታች የውሀ አቅርቦትና ስነ-ንጽህና በትምህርት ቤቶች ....................23
6. አካታች የውሀና ስነ-ንጽህና አገልግሎት በጤና ተቋማት ....................25
7. የባለድርሻ አካላት ሚናና ኃላፊነት ....................27
8. ስለአካታችነት መዘንጋት የሌለባቸው ነጥቦች ....................29

በእዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉት ስዕሎች በሙሉ የአዲስ አበባ ነዋሪ በሆኑትና የመስማት ስነት ባለባቸው አርቲስት በአቶ ተስፋዬ መንክር የተሳሉ ናቸው፡፡

## 1. አካታችና ለሁሉም ተደራሽ ውሃ፣ የአካባቢና የግል ንጽህና

ይህ መመሪያ በቀበሌና በማህበረሰብ ደረጃ ላሉ በንፁህ ውሀ የአካባቢና የግል ንፅህና አቅርቦት የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን አላማውም የውሃ፣ የአካባቢና የግል ንጽህና ስራዎች ከእቅድ አንስቶ እስከ አስተዳደር ድረስ አካታችና ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡ የቀበሌ የውሃ፣ የአካባቢና የግል ንጽህና ቡድን፣ የትምህርት ቤት አስተዳደር፣ የጤና ተቋማትና የጤና ኤክስቴንሽን፣ የሴቶች የልማት ሰራዊት፣ የወላጅና መምህራን ህብረትና የጤና ኮሚቴዎች፣ የማህበረሰብ ማህበራት፣ የእምነት ጠቋማትና የሃይማኖት መሪዎች፣ እንዲሁም የአካል ጉዳተኛ ሰዎች ማህበራት በዚህ ውስጥ ይካተታሉ፡፡ መመሪያው የተዘጋጀው በአካል ጉዳተኛ ሰዎች መብትና ፍላጎት ዙርያ ያለውን ግንዛቤ ለማስፋትና የየውሃ፣ የአካባቢና የግል ንጽህና የውሃ፣ የአካባቢና የግል ንጽህና አገልግሎት አካታችና ለሁሉም ተደራሽ ስለሚሆንበት ሊተገበር የሚችል ሁኔታ መረጃ ለመስጠት ነው፡፡

የአካል ጉዳተኛ ሰዎች በሁሉም ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ቢሆንም ከውሃና ከንጽህና አገልግሎት ተደራሽነት አኳያ ሰፊ ችግር የሚያጋጥማቸው በመሆኑ የዚህ መመሪያ ትኩረት እነሱ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን የውሃ፣ የአካባቢና የግል ንጽህና ተቋማትን ይበልጥ ተደራሽ ማድረግ ጥቅሙ ለአካል ጉዳተኛ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለህጻናት፣ ለነፍሰጡር ሴቶች፣ ለታመሙና ለአረጋውያን ረጅም ርቀት መጓዝ ለሚያዳግታቸው፣ መሸከም ለማይችሉና ባግባቡ ተቀምጠው መጸዳዳት የሚሳናቸውን ጨምሮ ለማንኛውም የማህበረሰብ አባል ነው፡፡ የንጹህ መጠጥ ውሃና፣ የአካባቢና የግል ንጽህና አገልግሎቶች ተጠቃሚ መሆን እንዲሁም የሁሉንም የማህበረሰብ አባላት ተሳትፎና አስተዋጽኦ የሁሉም ሰዎች መሰረታዊ መብት ነው፡፡

**ተደራሽነት** ማለት የምንገለገልበትን አገልግሎት መስጫ ተቋም ላለንበት አካላዊ ሁኔታ ተስማሚ የሆነ መግቢያና በቅርበትም ውስጡ ገብቶ ለመገልገል መቻል ነው፡፡ ተደራሽ አገልግሎት መስጫ የሚባለው ለአካል ጉዳተኛ ሰዎች ብቻ ተለይቶ የተዘጋጀ ማለት ሳይሆን፣ ማንኛውም የህብረተሰቡ አባል ሊገለገልበት የሚችል ማለት ነው፡፡

**አካታች ልማት** አላማው ሁሉንም ሰዎች በእኩልነት የሚያስተናግድ በበቂ ሁኔታ የሚያሳትፍና ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ እድል የሚሰጥ ማህበረሰብ መፍጠር ነው፡፡ በመሆኑም አካታችነት የአገልግሎት መስጫዎችን ተደራሽ ማድረግን ብቻ ሳይሆን፣ በውሃ፣ የአካባቢና የግል ንጽህና ስራዎች እቅድ አዘገጃጀት፣ አስተዳደር፣ አገልግሎት አሰጣጥና ጥገና ውስጥ የሁሉንም ተሳታፊነትና ተደማጭነት ማረጋገጥን ይጨምራል፡፡ በየውሀ የአካባቢና የግል ንጽህና አገልግሎት መስጫዎች በእኩል ደረጃ ተገልጋይ መሆን መቻልና በእቅድ ዝግጅት፣ በአስተዳደርና በጥገና ስራዎች ውስጥ መሳተፍ ለአካል ጉዳተኛ ሰዎች በጣም አስፈላጊ ነው፡፡



## 2. አካል ጉዳተኝነት ምን ማለት ነው?

**የአካል ጉዳትን** ለመተርጎምና ለመረዳት የሚጠቅሙን ሁለት ቁልፍ ፅንሰ ሀሳቦች ያሉ ሲሆን እነሱም **ስነት** እና **አካል ጉዳት** ናቸው። እነዚህ ሁለት ፅንሰ ሀሳቦች መካከል ጉልህ ልዩነት አለ። **ስነት** ሥር በሰደደ የጤንነት ጉድለት (ለምሣሌ የስኳር በሽታ)፣ በምግብ እጥረት፣ በህመም (ለምሣሌ የልጅነት ልምሻ፣ ወባ)፣ በጉዳት (ለምሣሌ የቤት ውስጥ አደጋ፣ የተሽከርካሪ አደጋ፣ ፀብ ወይም ግጭት፣ የቦምብ ፍንዳታ) የሚከሰት **የአካል መደበኛ ተግባር መስተጓጐልን ወይንም የአካል መዋቅር መዛባትን** ይመለከታል፡ ፡ ስነት በጽንስ/ በወሊድ ግዜ ወይም ከውልደት በኋላ በሂደት የሚፈጠር ነው። የሰዎችን የእለት ከእለት እንቅስቃሴ የሚወስኑ የስነት አይነቶች በርካታ ናቸው፡





**የመንቀሳቀሻ አካል ስነት፡** እንቅስቃሴ ማድረግንና ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወርን ያውካል። ለምሳሌ በመኖሪያ ቤት ውስጥ የመንቀሳቀስ ችግርን፣ ረጅም ርቀት መጓዝ ያለመቻልን፣ ደረጃ ለመውጣት መቸገርን፣ አጅን ለመዘርጋት ወይም ለመንበርከክ ያለመቻልን፣ እንዲሁም እጆችን ተጠቅሞ አንድን ነገር ለመያዝ ወይም ጣቶችን ለመጠቀም ማዳገትን ያካትታል።



**የማየት ስነት፡** አንድ ወይንም ሁለት አይኖቻቸው የተሰወረ ወይንም አጥርተው የማያዩላቸውን ሰዎች ያካትታል። አጥርቶ የማየት ችግር ያለበት ሰው የሚያውቃቸውን ሰዎች መልክ ወይንም የቁሳቁሶችን አይነት በጣም ተጠግቶ ካልሆነ በቀር ለመለየት አይችልም። ለእርሱ የሚታየው የነገሮች ቅርጽ ወይም ብርሃንና ጥላ ብቻ ነው።



**የመስማት ስነት፡** ጆሮዎቻቸው ፈጽሞ የማይሰሙ አልያም የአንዱ ወይም የሁለቱም ጆሮዎቻቸው የመስማት አቅም በከፍተኛ ደረጃ የቀነሰባቸውን ሰዎች ያካትታል። ለምሳሌ ተመሳሳይ ክፍል ውስጥ ወዲያኛው ጥግ ላይ ያለ ሰው የሚያሰማውን ልከኛ ድምጽ ለመስማት ይቸገራሉ። በጉዳታቸው መጠን የሚወሰን ሆኖ፣ የመስማት ስነት ያለባቸው ሰዎች በንግግር ወይንም በምልክት ቋንቋ ሊግባቡ ይችላሉ።





**የመናገር ስነት፡** በማንኛውም ቋንቋ ድምጽ በማውጣት የመናገርና የመግባባት ችግር ያለባቸውን ወይም የሌሎች ሰዎችን ንግግር ለመረዳት የሚቸገሩ ሰዎችን ያካትታል።

**የአይምሮ እድገት ውሱንነት፡** አዳዲስ ወይም የተወሳሰቡ መረጃዎችን የመረዳት አቅማቸው ውሱን የሆነ ወይንም አዲስ ሙያ የመማርና የመተግበር ክህሎታቸው አናሳ የሆኑ ሰዎችን ይመለከታል። ይህም የቋንቋና የማስታወስ ችሎታቸውን፣ከሌሎች ጋር የመግባባት ችሎታቸውን እንዲሁም እራሳቸውን የመንከባከብና ሃላፊነት የመውሰድ ብቃታቸውን ጭምር ሊጎዳው ይችላል።

**ስነልቦናዊ ስነቶች፡** ስር ከሰደደ የአይምሮ መታወክ ጋር የተያያዘ ሲሆን አመለ ቢስነትን፣ እራስን መጣልን፣ ግራ መጋባትንና የአይምሮ ጭንቀትን ሊያስከትል ይችላል። እነዚህ ችግሮች በተራቸው በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ የመሳተፍ ብቃታቸውን ይጎዱታል።

**የአካል ጉዳተኛ ሰዎች ጉዳት ለተራዘመ ግዜ አብሯቸው የሚኖር በመሁኑ በማህበረሰብ ውስጥ ባለ የተዛባ አመለካከት እንዲሁም በአካባቢያዊና በአሰራር በሚፈጠሩ መሰናክሎች የተነሳ በማህበረሰብ ውስጥ የተሟላና ሁለገብ ተሳትፎ ለማድረግ ይቸገራሉ፡፡**

በዓለም የጤና ድርጅት ግምት መሰረት በኢትዮጵያ ከ100 ሰዎች ውስጥ 18ቱ አንድ ዓይነት ስነት አለባቸው፡፡ ማንኛውም ዓይነት የአካል ስነት በሰው ልጆች መካከል ሊኖር የሚችል ራሱን የቻለ ማንነት ተደርጎ መወሰድ የሚገባውና በማናቸውም ጊዜ በማንም ላይ ሊደርስ የሚችል ናቸው፡፡ የአካል ጉዳት በሁሉም ጾታዎች፣ የእድሜ ክልሎች፣ ማህበረሰባዊ እርከኖችና የገቢ መጠን እንዲሁም በተለያዩ ብሄረሰቦች ውስጥ ይኖራል፡፡ የአካል ጉዳተኛ ሴቶች በተለይ ከፆታና ከአካል ጉዳተኝነት ጋር የተያያዘ ተደራራቢ ፈተና አለባቸው፡፡ በተነፃፃሪ የበለጠ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች በይበልጥ ለከፋ ጉዳት ይጋለጣሉ፡፡ ሆኖም የቤተሰብና የማህበረሰብ ድጋፍ፣ ትምህርትና ሀብት ካለ የእንቅስቃሴና የተሳትፎ መገደብን ለማቃለል ሊያግዙ ይችላሉ፡፡

የአካል ጉዳተኝነትን በምንለካበት ጊዜ ግለሰቡ የአካል ጉዳተኛ ስለመሆን አለመሆኑ ቀጥተኛ ጥያቄ ከማቅረብ ይልቅ ትኩረታችንን በአካል ጉዳቱ አይነትና ጉዳቱ ሰውየው የሚፈልገውን ነገር ለመፈጸም ያሉበትን ውሱንነቶች በመረዳት ላይ ማድረግ ይገባናል፡፡ ቀጥተኛ ጥያቄ ማቅረብ ሰውን የማሸማቀቅና ጉዳቱ ከተገለጸ በህብረተሰብ ውስጥ የሚፈጥረውን አድሎና ማግለል ከመፍራት የተነሳ አብዛኛውን ጊዜ ትክክለኛውን ምላሽ ማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

**ከሚከተሉት የአካል ጉዳቶች ውስጥ አንድ ወይንም ከአንድ በላይ ያለበት ሰው አካል ጉዳተኛ ይባላል፡**

**አንደኛው ወይንም ሁለቱም አይኖቹ በመነጽር እገዛ እንኳን ለማየት በጣም መቸገር**
ለምሳሌ፡ የሚያውቃቸውን ሰዎች መልክ ወይንም የቁሳቁሶችን ምንነት እጅግ በጣም ካልቀረቡት በስተቀር መለየት ያለመቻል
**በማዳመጫ መሳሪያ ታግዞ እንኳን ለመስማት በጣም መቸገር**
ለምሳሌ፡ ተመሳሳይ ክፍል ውስጥ ትንሽ ራቅ ብሎ የሚገኝ ሰው የሚያሰማውን ልከኛ ድምጽ ለመስማት መቸገር ወይንም የአንደኛው ጆሮ የመስማት አቅም ከሌላኛው በጣም ያነሰ መሆን
**ደረጃ ለመውጣትና ለመውረድ በጣም መቸገር**
ለምሳሌ፡ በመኖሪያ ቤት ው ስጥ የመንቀሳቀስ ችግር፣ ረጅም ርቀት መ ጓዝ ያለመ ቻል፣ ከቤት ወደ ውጭ ለመውጣት መቸገር፣ ረጅም ርቀት መጓዝ (ከ1 ኪ.ሜ በላይ) ያለመቻል፡፡
**ገላን ለመታጠብ ወይንም ልብስ ለመልበስ በጣም መቸገር**
**ከከፍተኛ የማስታወስ ችግር የተነሳ የእለት ተእለት ተግባርን ለማከናወን በእጅጉ መቸገር**
ለምሳሌ፡ አስፈላጊ እለታዊ ተግባራትን አስታውሶ ለማ ከናወን ያለመ ቻል፣ ወደተለመዱ ስፍራዎች የሚወስዱ አቅጣጫዎችን መዘንጋት፣ ወይም የሚቀርቧቸውን ሰዎች ስም ያለማስታወስ
**ለመናገር ወይም የሌሎችን ንግግር ለመረዳት (የምልክት ቋንቋን ጨምሮ) በጣም መቸገር**
ለምሳሌ፡ ሌሎች ሰዎች የሚናገሩትን ለመረዳት ይቸገራሉ ወይም እነሱ የሚናገሩት ለሌሎች ሰዎች ግልጽ አይሆንም
**ደጋፊ መሳሪያዎችን ለመጠቀም መገደድ**
ለምሳሌ፡ ክራንች፣ በእጅ የሚገፋ ጋሪ፣ ሰው ሰራሽ የሰውነት አካል፣ የሌላ ሰው ድጋፍ

የአካል ጉዳተኞችን በውሀና ንጽህና እንቅስቃሴዎች ውስጥከመሳተፍ ሊያግዷቸው የሚችሉ በርካታ መሰናክሎች አሉ፡፡ አብዛኞቹ በማህበረሰቡ ውስጥ ካሉ የተዛቡ አመለካከቶች እንዲሁም አካባቢያዊና ከአሰራር ውጫዊ ምክንያቶች ይመነጫሉ፡፡

አካል ጉዳተኛ ሰዎች ለእነዚህ መሰናክሎች ሲጋለጡ በማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በተሟላ መልኩ ለመሳተፍና አስተዋጽኦ ለማድረግ ይቸገራሉ፡፡ የአካል ጉዳኝነት ተብሎ የሚጠራውም ይህ ነው፡፡ መሰናክሎቹ ሲወገዱ አካል ጉዳተኛው ሰው ከሌሎች ጋር እኩል ተሳትፎ ማድረግ ይችላል፡፡



**የተዛባ አመለካከት** በአካል ጉዳተኛ ሰዎች ላይ ትልቁን ችግር የሚፈጥሩት የተዛቡ አመለካከቶች፣ የተሳሳቱ እምነቶች እና መድልዎ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ አካል ጉዳተኝነት እንደ አሳፋሪና አሳዛኝ ክስተት ተደርጐ ስለሚወሰድ መገለልን ወይም ከልክ ያለፈ ከለላ ማድረግን ያስከትላል፡፡ አንዳንድ ጊዜም አካል ጉዳተኝነት እንደ እርግማን ይቆጠራል፡፡ መድልዎን በመፍራት የአካል ጉዳተኛው ቤተሰቦች ግለሰቡን በቤት ውስጥ ተደብቆ እንዲቀመጥ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ የአካል ጉዳተኞች የውሃም ሆነ የአገልግሎት መስጫ ቦታዎችን እንዳይበክሉ በሚል የቤተሰብ ወይም የጋራ በሆኑ መጠቀሚያዎች እንዳይገለገሉ ሊታገዱ ይችላሉ፡፡



**ተፈጥሮአዊ መሰናክሎች** የሚባሉት ያልተስተካከሉ ወይም ጭቃማና አንሸራታች የሆኑ ተዳፋት መንገዶች ናቸው። አንዳንድ ጊዜ የእግር መንገዶችን ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም የሚያሰቸግሩ ሊሆኑ ይችላሉ። ለብዙዎች፣ የስብሰባ ቦታዎችም ሆኑ የውሃ ተቋማት የሚገኙባቸው ቦታዎች በጣም ሊርቁ፣ የንፅህና አገልግሎት መስጫዎች ጨርሶ ላይኖሩ ወይም ሊቆለፉ አሊያም አገልግሎት ሊሰጡ በማይችሉበት ደረጃ የንጽህና ጉድለት ሊኖርባቸው ይችላል።



**ከአስራር የሚመጡ መሰናክሎች** ከፍ ያሉ የደረጃ መርገጫዎች፣ ጠባብ በሮች፣ የመዝጊያዎች ያለመኖር ወይም በጣም መክበድ፣ ጠባብ ክፍሎች፣ በቂ ብርሃን ያለመኖር፣ የደረጃ መደገፊያ ያለመኖር እና የመሳሰሉትን ያካትታል።

በርካታ የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ልጆች ውሃና የንፅህና መጠበቂያ አገልግሎት መስጫዎች ባለመኖራቸው ወይም ለመጠቀም የሚያስቸግሩ በመሆኑ ምክንያት ከትምህርት ገበታ ይገለላሉ። ከትምህርት ቤቶች የመፀዳጃ አገለግሎት መስጫዎች ጋር በተያያዘ እንደ መሰናክል ሊቆጠሩ የሚችሉት የመፀዳጃ ጨርሶ አለመኖር ና፣ ወደ መፀዳጃዎች የሚወስዱ መንገዶች አመች አለመሆን፣ አጋዥ ወይም መሪ ወይም ደጋፊ ነገሮች አለመኖር ወይም የክፍል መጥበብ ሊሆኑ ይችላሉ።

## 3. በንጹህ ውሀ የአካባቢ እና የግል ንጽህና ፕሮጀክቶች እቅድ ዝግጅት፣ አስተዳደር፣ ኦፕሬሽንአገልግሎት አሰጣጥና ጥገና ላይ ሁሉአቀፍ ተሳትፎ፣ አስተዋጽኦና አካታችነት

የአካል ጉዳተኛ ሰዎች ከሌሎች ሰዎች እኩል የልማት ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው ይህም የውሃና ንጽህና አገልግሎትን፣ ትምህርትን፣ የጤና አገልግሎትን፣ ወዘተ… ይጨምራል፡፡ አካል ጉዳተኞች ለሚኖሩበት ማህበረሰብና ለቤተሰቦቻቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ፣ እንደማንኛውም ሰው የተሟላ መብት ያላቸው የህብረተሰብ አባላት መሆናቸው እውቅና ሊሰጠው ይገባል፡፡ የኢትዮጵያ ህገመንግስትና በርካታ ብሄራዊና ዓለምአቀፋዊ ህጎች ይህን መብት ያጎናጽፏቸዋል፡፡ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች እንደ ተመጽዋች፣ በህክምና መፍትሄ የሚፈልጉ ብቻ ተደርገው የከካል ጉዳታቸው ተጠቂ ሆነው ሊታዩ አይገባም፡፡



**አካል ጉዳተኛ ሰዎች የውሀና የንጽህና አቅርቦትን በማስተዋወቅ፣ በማቀድ፣ በማስተዳደር፣ በአገልግሎት አሰጣጥና ጥገና ዙሪያ የሚካሄዱ ስብሰባዎችና እንቅስቃሴዎች አካል መሆን አለባቸው፡፡**

ከውሀና ንጽህና ኮሚቴ አባላት እና ከማንኛውም ጤና ኮሚቴ ለምሳሌ (ከሲ.ኢ.ል.ቲ.ኤስ.ኤች) ኮሚቴ መሃከል ቢያንስ አንዱ የተወሰነ ዓይነት የአካል ጉዳት ያለበት ሰው ሊሆን ይገባል፡፡

የአካል ጉዳተኛ ሰዎች ከማንኛውም የህብረተሰብ አባል ያልተናነሰ አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ገንዘብ በማዋጣት፣ በግንባታ ስራ በመሳተፍ (ቁሳቁስ በመሸከም፣ የኮንስትራክሽን ሰራተኞችን በልዩልዩ መንገድ በማገዝ፣ ወዘተ)፣ መረጃ በመመዝገብ፣ ንብረት በመጠበቅ፣ ለኮንስትራክሽ ሰራተኞች መጠለያ ወይም ምግብ በመስጠት፣ ወዘተ፡፡

በተጨማሪም የአካል ጉዳተኛ ሰዎች በጽህፈት ስራ፣ በንብረት እንክብካቤ፣ በጥበቃ፣ በገንዘብ ያዥነት፣ በኮሚቴ አባልነት፣ ወይም በውሃ ሻጭነት በመሳተፍ የዉሀና ንጽህና አመራር አካል በመሆን ማገልገል ይችላሉ፡፡

ከአር ነጻ ቀበሌን ከሚያረጋግጠው ቡድን ውስጥ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች ተወካዮችን በማካተት ተሳትፎአቸውን ማረጋገጥ ያሻል፡፡ ቡድኑ አካል ጉዳተኛ የሆኑ የማህበረሰቡ አባላት ከአካባቢና የግል ንጽህና ስራ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆናቸውን ማረጋገጥም ይጠበቅበታል፡፡





**ጥቃቅንና አነስተኛ የግል ንግድ ማህበራት** የንጹህ መጠጥ ውሃ፣ ሳኒቴሽንና ሃይጅን አቅርቦትን ለማሻሻል በወረዳ ደረጃ ይቋቋማሉ፡፡ ማህበራቱ ለምሳሌ በስነ-ንጽህና ግብይት፣ በመለዋወጫ ቁሳቁስ አቅርቦት እና/ወይም በውሀና ስነ-ንጽህና ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥና ጥገና ላይ የሚሰሩ ናቸው፡፡
አካል ጉዳተኛ ሰዎች በሙሉ አቅማቸው እንዲሳተፉ ለማስቻልና ከሌሎች የማህበረሰቡ አባላት እኩል የልማት ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ ሲባል በማህበራቱ. ውስጥ በአባልነት እንዲታቀፉ ማድረግ ይገባል፡፡ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ከኢኮኖሚ ጥቅሞች የተገለሉ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን ለሌሎች አርአያ ስለሚሆኑና ሙሉ የህብረተሰብ አካል መሆን ስለሚያስችላቸው ለአካል ጉዳተኛ ሰዎች የስራ እድል መፍጠር በጣም ይጠቅማል፡፡
እያንዳንዱ ማህበር ቢያንስ አንድ የአካል ጉዳተኛ (ሴት ብትሆን ይመረጣል) አባል ሊኖረውና አካል ጉዳተኞች የቢዝነስ እቅድ በማውጣት፣ በማምረት ሂደትና በሽያጭ ላይ እኩል ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
በተጨማሪም በስነ-ንጽህና ግብይት የሚሳተፉ አነስተኛና ጥቃቅን ማህበራት የቤተሰብ ወይም የገጠር ትምርት ቤቶችና ጤና ተቋማት መጸዳጃ ቤቶችን ተደራሽነት የሚያሻሽሉ የመጸዳጃ ቤት መቀመጫዎች፣ የእጅ መደገፊያዎች፣ ወዘተ… ማስተዋወቅ፣ ማምረትና መግጠም ይችላሉ፡፡ በዚህ መንገድ፣ ቀበሌዎችና ወረዳዎች ከአር ነጻ የመሆን ግባቸውን ለማሳካት በሚያደርጉት ጥረት ውስጥ አነስተኛና ጥቃቅን ማህበራት ለት/ቤቶች፣ ለጤና ተቋማት፣ ለቤተሰብና ለህዝባዊ ድርጅቶች የመጸዳጃ ቤቶችን ተደራሽ በማድረግ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡

## 4. የማህበረሰብ ዉሀ አቅርቦትና ስለ-ንጽህና አካታች መፍትሔዎች

**ተስማሚ አካታች መፍትሄዎች ወይንም አሰራሮች የአካል ጉዳት ባለባቸው ፍላጎት ላይ የሚ መሰረቱ በመሆኑ በዚህ ክፍል ውስጥ ዝርዝር መለኪያዎች አይቀርቡም፡፡ የዚህ ርዕስ ዋና አላማ አካል ጉዳተኛ ሰዎች የማንንም ድጋፍ ሳይሹ ወይንም በአነስተኛ ድጋፍ ብቻ የውሀና የስነ-ንፅህና ተቋማትን መገልገል እንዲችሉ ማገዝ ነው፡፡**



**ወደ ተቋማት መዳረሻ መንገዶች**

ማንኛውም የቤተሰብና የማህበረሰብ አባል አካል ጉዳት ያለባቸውን ጨምሮ የመጠጥ ውሀና የመጸዳጃ ተቋማትን ለመጠቀም የሚገኙበት ቦታ መድረስ መቻል አለባቸው፡፡ መጸዳጃ ቤቶችና የውሃ አቅርቦት ተቋማት በተቻለ መጠን ለተገልጋዩ በቅርብ ርቀት ላይ መገኘት አለባቸው፡፡ የቤተሰብ መጸዳጃ ቤቶች ከመኖሪያ ቤት ያላቸው ርቀት ከ15 ሜትር ባይበልጥ ይመረጣል፡፡

**ወደ አገልግሎት መስጫ የሚወስድ መንገድ፡**

ወደ መጸዳጃ ቤት የሚወስድ መንገድ አባጣ ጎርባጣ የሌለው ሆኖ የማያዳልጥ መሆን ይኖርበታል (ለምሳሌ የጠጠር መንገድ ቢሆን)፡፡ እንደ ሳርና ቁጥቋጦ ያሉ አደናቃፊዎችን መቁረጥ፣ ጉድጓዶችን መድፈን እና ትላልቅ ድንጋዮችን ማንሳት ያስፈልጋል፡፡ መንገዱ ቢያንስ የ90 ሳሜ ስፋት ሊኖረው ይገባል፡፡ በመንገዱ ጠርዞች ድንጋይ በመኮልኮል ወይም በነጭ ቀለም በማስመር ምልክቶች እንዲኖሩት ማድረግና የማየት ስነት ላለባቸው ደግሞ መሪ ገመድ መዘርጋት ይጠቅማል፡፡ ድንጋዮች ወይም ገመድ ተገልጋዮችን ወደሚፈልጉት ስፍራ ለመምራት ይረዳሉ፡፡ ነጭ ቀለም ደግሞ የማየት አቅማቸው ውሱን የሆኑ ሰዎች የቀለም ልዩነቱን እየተጠቀሙ መንገዱን እንዲለዩ ያግዛቸዋል፡፡፡

**መወጣጫ ደረጃዎች፡** ወደተቋማት ለመድረስ የሚሰሩ ደረጃዎች ተመሣሣይ ከፍታና ርዘመት ኖሯቸው፣ የተቀራረቡ፣ ሰፋፊና ገፃቸው የተስተካከለ መሆን አለበት። የደረጃው ስፋት ከ30 ሳሜ ያላነሰና የእያንዳንዱ ደረጃ ከፍታ ከ16 ሳሜ ያልበለጠ መሆን አለበት።

**የእጅ መደገፊያዎች፡** ሚዛን ለመጠበቅ እንዲረዳ ለደረጃዎቹ የእጅ መደገፊያ በ70 - 90 ሳሜ ከፍታ መሥራት ይቻላል። ብዙ ተጠቃሚዎች በተለይ የእጅ መደገፊያ ካለ ያልተራራቁና የተስተካከሉ ደረጃዎችን መጠቀም ሳያዳግታቸው ይችላል።





**በደረጃ ምትክ የሚሰራ ራምኘ፡**

ተሽከርካሪ ወንበር ለሚጠቀሙ ብቻ ሳይሆን ምርኩዝ ለሚጠቀሙ፣ የመራመድ ችግርና ዓይነ ስውርነት ላለባቸው ሁሉ ጠቃሚ ናቸው፡፡ አስፈላጊነቱ ከታመነበትና በቂ ቦታ ካለ ወደ አገልግሎት መስጫው የሚወስድ ራምኘ ቢቻል የእጅ መደገፊያ እንዲኖረው ተደርጎ ሊሠራ ይችላል፡፡ በደረጃዎች ምትክ የሚገባው ራምፕ ተዳፋትነት ከ8 በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡ ይህ ማለት ለ10 ሳሜ ተዳፋትነት የራምፑ ርዝመት 1 ሜትር ይሆናል ማለት ነው፡፡ ከውሃ መቅጃው ወይም ከመፀዳጃ ቤቱ ፊት ለፊት ቢያንስ ከ100 እስከ 120 ሳሜ ርዝመት ያለው የተስተካከለ የራምፕ መውረጃ ቦታ ያስፈልጋል፡፡ መውረጃው(ራምፑ) ቢረጥብም እንኳን አዳላጭ መሆን የለበትም ሸካራ ወለል ሊሆን ይገባል፡፡ ራምኘ ከማንኛውም ጠንካራ ከሆነ በአካባቢ ከሚገኝ  እንደ እንጨት፣ ቀርከሃ፣ ድንጋይ ወይም ሲሚንቶ የመሳሰሉ ነገሮች ሊሠራ ይችላል፡፡ ራምኘ በአንድ ቦታ ላይ ቋሚ ወይንም ሊነሳ የሚችል ተደርጎ ሊሰራ ይችላል፡፡



**መግቢያ በሮችና ደጃፎች፡** በምንጸዳዳበት ወቅት ከዕይታ ለመከለል መዝጊያ በሮች መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ የመጸዳጃ ቤቱ በርና ሌሎች መግቢያዎች ሰፊ መሆን አለባቸው፡፡ የበሮች ስፋት ቢያንስ 90 ሳ.ሜ ሲሆን ከደጃፉ ጋር የከፍታ ልዩነት የሌለው ወይም አነስተኛ ልዩነት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡ በቀላሉ ሊከፈትና ሊዘጋ የሚችል ሆኖ በአካባቢው ከሚገኙ እንደ ጨርቅ፣ እንጨት እና ቆርቆሮ ከመሳሰሉ ነገሮች ሊሠራ ይችላል፡፡ ለአካል ጉዳተኞች ተብሎ የሚሰሩ በሮች የሚከፈቱት ወደ ውጭ መሆን አለበት፡፡ ወደ ውስጥ የሚከፈት ከሆነ ግን ተሽከርካሪ ወንበሩ ከገባ በኋላ በሩን ዘግቶ መጠቀም ያስቸግራል፡፡

**ወለሎች፡** በተለይ በአጋዥ መሣሪያዎች እጦት ምክንያት ለሚድሁ የአካል ጉዳተኞች ሲባል ወለሎች ለስለስ ያሉ ነገር ግን አዳላጭ ያልሆኑ፣ በቀላሉ ለማጽዳት የሚያመቹ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ሰው የመጸዳጃ ቤቱን ከተጠቀመ በኋላ ንጹህ አድርጎ መውጣት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

**ብርሃን፡** የብርሃን በበቂ ሁኔታ መኖር በተለይ የማየት ችሎታቸው ለቀነሰ ሰዎች አስፈላጊ ነው፡፡ መጸዳጃ ቤቶች ቀላል የሶላር ወይም የመስመር መብራቶች ሊገባላቸው ይገባል፡፡





**የእጅ መደገፊያዎች፡** የመፀዳጃ ቤቱ መቀመጫ ላይ ለመድረስና ለመቀመጥ ድጋፍና ሚዛን መጠበቂያ እንዲሆኑ ጠንካራ የእጅ መደገፊያዎች /ብረት፣ እንጨት ወይም ቀርከሃ/ እወለሉ ላይ ሊተከሉ ወይም ከመቀመጫው ጎን ከ70 እስከ 90 ሳሜ ከፍታ ኖሯቸው ግድግዳው ላይ ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ የሚገጠሙበት ቦታና ከፍታ የተጠቃሚዎቹን ሁኔታ በማጥናት የሚወሰን ይሆናል፡፡ ለዓይነ ስውራን ሰዎች የመፀዳጃው ጉድጓድ/መቀመጫው ያለበትን ቦታ መለየት ይችሉ ዘንድ የሚዳሰሱ ምልክቶች ሊያስፈልጓቸው ይችላሉ፡፡ (ለምሣሌ በግድግዳው ወይም በወለሉ ላይ መቀመጫው ያለበትን ቦታ የሚያመለክቱ ምልክቶች  ማበጀት)፡፡

**የበር እጀታዎችና መሽጎሪያ/መቆለፊያዎች፡** የሁሉንም ተጠቃሚዎች በተለይም ደግሞ የሴቶችንና የልጃገረዶችን ደህንነትን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ውድ ያልሆኑ አማራጮች ከእንጨት የሚሰሩ መያዣዎች ሲሆኑ አብዛኛው ጊዜ ከወለል ከ90 እስከ 120 ሳሜ. ከፍ ተደርገው ይሰራሉ፡፡ በሩ ሙሉ ለሙሉ ወደውጭ የሚከፈት ይሆንና የሚገፋ ተሽከርካሪ ወይም ክራንች ለሚጠቀሙ ወይም የእጅ ጥንካሬአቸው ደካማ ለሆነ ሰዎች አጠቃቀም ያመች ዘንድ በውስጥና በውጭ በኩል መያዣዎች ይበጁለታል፡፡





**የመፀዳጃ ቤት መቀመጫዎች፡** የመፀዳጃ ቤት መቀመጫዎች ነፍሰጡሮችን፣ አረጋውያንን እና የአካል ጉዳተኛ ሰዎችን ጨምሮ ቁጢጥ ብለው መቀመጥ ለሚቸገሩ ሰዎች ሁሉ ተስማሚ ሊደረጉ ይገባል። መቀመጫው የማይንቀሳቀስ ወይም አንዳንድ የቤተሰብ አባላት ቁጢጥ ማለትን የሚመርጡ ከሆነ ተንቀሳቃሽ ሊሆን ይችላል።

ለገጠር መኖሪያ ቤቶች በአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች /እንጨት፣ ቀርከሃ፣ ኘላስቲክ/ የሚሠራ ተንቀሳቃሽ መቀመጫ ውድ ያልሆነና ቀላል አማራጭ ነው። መቀመጫውን ለማጽዳት ምቹ እንዲሆን ወይም ጥንካሬ እንዲኖረው ቀለም ወይም ቫርኒሽ መቀባት ይቻላል። የዚህ ዓይነቱ መቀመጫ በመኖሪያ ቤት መፀዳጃ ቤት ጉድጓድ ላይ በማስቀመጥ ወይም ባልዲ ላይ በማስቀመጥ ጭምር መጠቀም ይቻላል። ሁለተኛው አማራጭ ለተጠቃሚው ከእይታ የመከለል ነጻነት ላይሰጥ ቢችልም እጅግም መንቀሳቀስ ለማይችሉ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ፈሳሽ ወደ ውጭ እየተረጨ አካባቢውን እንዳያቆሽሽ ከአሮጌ የፕላስቲክ ጠርሙሶች የተሰራ መከላከያ ከወንበሩ ፊት ለፊት ማያያዝ ይቻላል። የፕላስቲክ ጠርሙሶችን በመሰንጠቅ በወንበሩ የፊት እግሮች ላይ በማሰር የወንበሩን ፊትለፊት መሸፈን ይቻላል።




**እጅን መታጠብ፡** በመኖሪያ ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በቤተሰብ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ ከፍታው ከ50 - 90 ሳሜ የሆነ የእጅ መታጠቢያ ከውሃና ከሣሙና ጋር ከመፀዳጃ ቤት አጠገብ መኖር አለበት፡፡ ትናንሽ ጀሪካኖች ወይም የኘላስቲክ ጠርሙሶች ውሱን አቅም ላላቸው ወይም አንድ እጅ ብቻ ለሚጠቀሙ ሰዎች ውድ ያልሆኑ አማራጮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የእጅ መታጠብያው አካባቢ እንዳይጨቀይና እንዳያዳልጥ አሸዋ ወይም ባልዲ ከስር ማስቀመጥ ይቻላል፡፡





**የገላ መታጠቢያ ሥፍራዎች፡** ከእይታ ከለላ የሚሰጡና በቀላሉ ተደራሽ መሆን አለባቸው፡፡ አስፈላጊ ከሆነ ለረዥም ሰዓት መቆም ለማይችሉ /ሚዛናቸውን መጠበቅ ለማይችሉ፣ የመንቀሳቀስ ውሱንነት ላለባቸው፣ ለታመሙና እርግዝናቸው ለገፋ ሴቶች/ ከአካባቢው ከሚገኙ እንደ እንጨትና ድንጋይ ከመሳሰሉ ነገሮች የተሠሩ መቀመጫዎችን በተጨማሪነት ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ለተጠቃሚው እንዲመች መታተቢያው ከፍ ተደርጐ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ይህ ቀላልና ርካሽ አማራጭ ነው፣ ነገር ግን ሳፋውን በውሃ ለመሙላት የሌሎችን ዕርዳታ ሊያስፈልግ ይችላል፡፡

**የመኖሪያ ቤት የመጠጥ ውሀ፡** ውሱን አቅም ላላቸው፣ ሚዛናቸውን መጠበቅ ለሚሳናቸውና አንድ እጅ ብቻ ለሚጠቀሙ እንዲያመች የመጠጥ ውሃ ጥብቅ ክዳን ባለው ባልዲ ውስጥ በመጨመር ከሥሩ መክፈቻና መዝጊያ አበጅቶ መጠቀም ይቻላል፡፡

**ንጽህና፡** ሁሉም የንጹህ መጠጥ ውሀና ስነ-ንጽህና ተቋማት በተቻለ መጠን በንጽህና ሊያዙ ይገባል፡፡ በተለይም የመንቀሳቀሻ አካል ጉዳት|ለላባቻ ወይም ዓይነ ስውር ሰዎች ከሌሎች በበለጠ መልኩ የተቋሞቹን ልዩ ልዩ አካላት ለመንካት ስለሚገደዱ የንጽና ጉዳይ ለእነሱ ወሳኝ ነው፡፡



**የውሃ ተቋሙ ግንብ፡** በመወጣጫ ራምፕ አማካኝነት ወደ ውሀ መቅጃው ስፍራ መድረስ የሚያስችል በግቢው ውስጥ በተለይ ለተሽከርካሪ ወንበር ተጠቃሚዎች ለመዘዋወሪያ በቂ ቦታ ሊኖረው ይገባል፡፡ መግቢያው ሰፊና የማይጎረብጥ ነገር ግን አዳላጭ ያልሆነ መሆን አለበት፡፡ የውሃ ጣቢያውን ዙሪያ ማጠር ካስፈለገ አጥሩ ወደ ራምፑ መዳረሻዎችን ለመጠቀም የሚያግድ መሆን የለበትም፡፡ አጥሩ ሰዎች ወደ ውሀ ጣቢያው በቀላሉ እንዳይደርሱ መሰናክል መሆን የለበትም፡፡

**ጄሪካን ማሳረፊያ፡** የውሃ ጄሪካንን አንስቶ ለመሸከም እንዲያመች ከመሬት 70 ሳሜ ገደማ ከፍ ብሎ ከውሀ መቅጃ መክፈቻና መዝጊያ ወይንም በእጅ ፓምፑ አጠገብ ለጀሪካን ማሳረፊያ ግንብ ይገነባል። ይህም ለአቅመ ደካሞችና ሸክማቸውን አስተካክለው ለመሸከም ወይም ለመያዝ ለሚቸገሩ ሰዎች በጣም አስፈላጊ ሲሆን የግንባታ ዋጋውም አነስተኛ ነው።




የምንጭ ውሃን በሚመለከት፣ መደበኛው የቧንቧውን ውሀው መክፈቻና መዝጊያ የሚገኙበትን 70 ሳሜ ከፍታ ለሚረዝምባቸው ሰዎች ሲባል የተለያየ ከፍታ መጠቀም ይቻላል። ለምሳሌ አንዱን መውረጃ ቧንቧ ወደታች በማጠፍ ወደ 50 ሳሜ ዝቅ ማድረግ ይቻላል።

የተሽከርካሪ ወንበር ወይንም የክራንች ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች የመንንቀ መሳሪያዎቻቸውን ለውሃ ማመላለሻነት ሊጠቀሙ ይችላሉ። ተሽከርካሪ ወንበሩ ላይ እግር ማሳረፊያው አካባቢ ጄሪካን ማስቀመጥ የሚቻል ሲሆን የተሽከርካሪ መገልበጥ እንዳያጋጥም ሲባል ጄሪካኑን ሙሉ በሙሉ በውሃ መሙላት አያስፈልግም። በሌላ በኩል ደግሞ ክራንች ላይ ምስማር በመምታት አነስተኛ ጄሪካን ማንጠልጠል ይቻላል።

ውሃ ጣቢያ ድረስ መጥተው መቅዳት የማይችሉ ሰዎች ካሉ ወይንም በመሬቱ አቀማመጥ የተነሳ ወደ ውሃ ጣቢያው መዳረሻ መንገድ  መስራት ካልተቻለ ውሃ ወደ መኖሪያ ቤቶች ሊመጣ የሚችልባቸውን አማራጭ መንገዶች ማቀድ ይገባል። ለምሳሌ፡ እስከ መኖሪያ ቤት ድረስ ቧንቧ መዘርጋት፣ አነስተኛ የሶላር ወይም የኤሌክትሪክ ፓምፕ ምንጩ ላይ መትከል፣ የጣራ ውሃ መሰብሰብ፣ የግቢ ውስጥ የውሃ ጉድጓድ፣ የቤት ውስጥ የውሃ ማጣሪያ ዘዴን በተጨማሪ በመተቀም፣ ወዘተ።

## 5. አካታች የውሀ አቅርቦትና ስነ-ንጽህና በትምህርት ቤቶች

የትምህርት ቤቶች የውሀ አቅርቦትና ንጽህና አገልግሎት መስጫዎች ለሁሉም ተማሪዎችና መምህራን ተደራሽ በሚሆኑበት መልኩ መዘጋጀት አለባቸው፡፡ የውሀ አቅርቦትና ስነ-ንጽህና አገልግሎት የሁሉም ሰዎች መሰረታዊ ፍላጎት ከመሆኑም በላይ በሽታን ይከላከላል፣ የመማር ማስተማር ሂደትን ያሻሽላል፡፡ ተደራሽ የውሀ አቅርቦትና ስነ-ንጽህና አገልግሎት በሌለበት ሁኔታ አካል ጉዳት ያለባቸው ልጃገረዶችና ወንዶች ተማሪዎች አመቺ መጸዳጃ ቤት ስለማያገኙ ምግብ ከመብላትና ከመጠጣት ሊታቀቡ ይችላሉ፡፡ ይህም የጤና መዛባት ከማስከተሉም በላይ ውሎ አድሮ ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ ምክንያት ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ት/ቤቶች ለሚገኙበት ህብረተሰብ የውሀ አቅርቦትና ስነ-ንጽህና አጠባበቅ አርአያ ሆነው መገኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡




የትምህርት ቤት የውሃ አቅርቦት ተቋም የሚገነባው በት/ቤቱ ቅጥር ጊቢ ውስጥ ወይም ከቅጥር ጊቢው ከ100 ሜትር ባልበለጠ ርቀት ውስጥ ሆኖ በደንብ የተደላደለና በግልጽ የሚታይ መዳረሻ መንገድ ያለው መሆን አለበት፡፡ የውሃ ተቋሙም ሆነ የውሀ መቅጃዎቹ መክፈቻና መዝጊያ ለሁሉም ተደራሽ መሆን አለባቸው፡፡ የእጅ መታጠቢያዎች በተለያዩ ከፍታዎች ላይ /ከ50-70 ሳሜ/ ለመማሪያ ክፍሎች ቀረብ ብለው የሚገነቡ ሲሆን ያሉበት ቦታ የተስተካከለ ከጭቃማነትና ከአዳላጭነት የፀዳ መሆን አለበት፡፡



የትምህርት ቤት መጸዳጃ በት/ቤቱ ቅጥር ጊቢ ውስጥ ወይም ከቅጥር ጊቢው ከ30 ሜትር ባልበለጠ ርቀት ውስጥ መገኘት አለበት፡፡ ወደ መጸዳጃ ቤት የሚወስደው መንገድ በደንብ የተደለደለና የአካል ጉዳተኛ ሰዎች ጭምር በቀላሉ ሊጠቀሙበት የሚችል መሆን ይኖርበታል፡፡ በሁሉም ት/ቤቶች ለወንድ ተማሪዎች፣ ለልጃገረዶች፣ ለሴትና ለወንድ መምህራን ቢያንስ ቢያንስ አንዳንድ ለአካል ጉዳተኞች የተለዩ ክፍሎች ሊኖርና ክፍሎቹም ተደራሽ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ይህም ማለት መወጣጫ ራምፕ፣ ሰፊ በር (90 ሳሜ)፣ የተሽከርካሪ ወንበር ተጠቃሚውን ወይም ረዳቱን አንደልብ የሚያዘዋውር ሰፊ ቦታ (1.5ሜ x 2ሜ)፣እንዲሁም የእጅ ድጋፍና ከፍ ያለ መቀመጫ ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡ በሮቹ የሚከፈቱት ወደ ውጭ መሆን አለበት፡፡





መጸዳጃ ቤቶቹ ንጹህ፣ ሽታ አልባና በትምህርት ቀናት ሁሉ ክፍት መሆን መቻል አለባቸው፡፡

የእጅ መታጠቢያዎች ለሁሉም ልጆችና መምህራን ተደራሽ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ከመጸዳጃ ቤት አጠገብ የሚገነቡ ሲሆን የቧንቧ መክፈቻዎቹ ሁሉም ሰው ሊደርስበት የሚችል ከፍታ ሊኖራቸውና አካባቢው ጨቅይቶ እንዳያዳልጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በትምህርት ቤቶች **የወር አበባና ንፅህና** አገልግሎት መስጫዎች ክፍሎች ለአካል ጉዳተኛ ልጃገረዶችም ተደራሽ መሆን አለባቸው፡፡ መርሆዎቹ ከትምህርት ቤት መፀዳጃ ቤቶች ጋር ተመሣሣይ ናቸው፡፡ ወደ መፀዳጃው የሚወስደው መንገድ የተስተካከለና ምልክት የተደረገበት፣ መግቢያውም ለሁሉም ተደራሽና በቂ ስፋት ያለው መሆን አለበት፡፡

የት/ቤት ዋሽ ክለቦች የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን በአባልነት ማቀፍ ያለባቸው ሲሆን የክለቡ አባላት በውሀና በስነ-ንጽህና አገልግሎት ተደራሽነትና አካታችነት ዙርያ ሊወያዩ ይገባል፡፡

የትምህርት ቤት የውሀና ስነ-ንጽህና  አገልግሎት መስጫዎችን ውጤታማ ለማድረግ የሁሉም ተሳትፎ ያስፈልጋል- አካል ጉዳተኛ ልጆችንና የወላጆቻቸውን ጨምሮ፡፡ የሚካሄደው የግንባታ ቁጥጥር የአገልግሎት መስጫዎቹ አካታች ንድፍ  የተከተሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 6. አካታች የውሀና ስነ-ንጽህና አገልግሎት በጤና ተቋማት

በጤና ተቋማት የሚገኙ የውሀና ስነ-ንጽህና አገልግሎት መስጫዎች ለአካል ጉዳተኛ ሰዎች፣ ለነፍሰ ጡርና በቅርብ ጊዜ ለወለዱ ሴቶች፣ ለአረጋውያንና በህመም ለደከሙ ሰዎች ተደራሽ መሆን አለባቸው፡፡ አገልግሎቱ የሁሉም ሰዎች መሰረታዊ ፍላጎት ከመሆኑም በላይ የበሽታዎችን ስርጭት የመከላከያ መሳሪያ በመሆኑ የጤና ተቋማት ለሚገኙበት ህብረተሰብ በውሀ አቅርቦትና በስነ-ንጽህና አርአያ ሆነው መገኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከፍ ብሎ ት/ቤቶችንና የመኖሪያ ቤቶችን አስመልክቶ ከተጠቀሱት የተደራሽነት መርሆች ውስጥ አብዛኛዎቹ ለጤና ተቋማትም ጭምር ያገለግላሉ፡፡

ወደ መጸዳጃ ቤትና ወደ ውሃ ጣብያ የሚወስዱ መዳረሻ መንገዶች የተስተካከሉና መሰናክሎች የተወገዱላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡
የአገልግሎት መስጫዎቹን የግንባታ ቦታ አመራረጥ በተመለከተ ታካሚዎች ወደ መፀዳጃ ቤቱ ለመድረስ ብዙ እንዳይጓዙ ከጤና ጣብያው/ኬላው ህንጻ በጣም መራቅ የለበትም፡፡ ይህም የአካል ጉዳተኛ ሰዎችንም ይጠቅማል፡፡

ካሉት የወንድና የሴት መጸዳጃ ክፍሎች ውስጥ ቢያንስ አንድ ክፍል ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መደረግ አለበት፡፡ ክፍሉ **ከሌሎቹ ክፍሎች ጋር ሲነጻጸር ባለ 1 ሜትር ስፋት እና ወደውጭ የሚከፈት በር አለው፣ የተስተካከለ** መግቢያ ወይም ራምፕ (130 ሳሜ ስፋት፣ 6% ተዳፋትነት) አሉት፣ መግቢው ከብረት ቧንቧ የተሰሩ **የእጅ መደገፊያዎች** በጎንና ጎን ይኖሩታል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ከመጸዳጃ ቤቱ አጠገብ የሚገኘው የእጅ መታጠቢያ ከፍታው ለሁሉም ተደራሽ ይደረጋል፡፡ የቧንቧ መክፈቻዎቹ ሁሉም ሰው ሊደርስበት የሚችል ከፍታ ሊኖራቸው ይገባል፣ አካባቢው እንዳይጨቀይና እንዳያዳልጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

በተመሣሣይ መልኩ፣ የጤና ተቋሙ **የውሃ ማሰራጫዎች፣ የልብስ ማጠቢያ** ገንዳዎችና **የገላ መታጠቢያ** ክፍሎች ለሁሉም ተደራሽ ይሆኑ ዘንድ ራምፕ፣ ሰፋፊ በሮችና በተለያየ ከፍታ የተሠሩ የቧንቧ መክፈቻና መዝጊያዎች እንዲኖሯቸው ያስፈልጋል፡፡








ከ 1" የ ብረት ቧንቧ ወይም ከተሟሳሳይ ቁስ የተሰራ የእጅ መደገፊያ

ባለ 1" የ ብረት ቧንቧ በ30 ሳሜርቀት የተከፋፈለ

ለጥ ያለ ወይም ተዳፋትነቱ ከ6% ያልበለጠ ራምፕ መወጣጫ



## 7. የባለድርሻ አካላት ሚናና ኃላፊነት

**የቀበሌ ዉሃ አቅርቦትና ስነ-ንፅህና ቡድን (የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ፤የልማት ጣቢያ ሰራተኞች፣ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ የውሃ ቴክኒሻኖች፣ አዛውንቶች ፣ የማህበረሰብ መሪዎች፣ መምህራን፣ ወጣቶች፤በጐ ፈቃደኞች፣ የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ተወካዮች፤የአካል ጉዳተኞች ተቋማት) ሚናና ኃላፊነት፡**

- የማህበረሰቡ አባላት የሚከተሉትን እንዲገነዘቡ ማድረግ፡
  - የአካል ጉዳተኛ ሰዎች ወይም ቤተሰቦቻቸው በንፁህ መጠጥ ውሀ አቅርቦትና ስነ-ንፅህና ኮሚቴዎች ምርጫ ውስጥ ሊካተቱና ቅድምያም ሊሰጣቸው እንደሚገባ
  - አካል ጉዳተኛ ሰዎች በውሀና መጽዳጃ ተቋማት እንክብካቤና ጥበቃ ስራ ላይ እንዲሰማሩ ቅድሚያ መስጠት
- አዳዲስ የዋሽ ተቋማት በሚገነቡበት ወይም አሮጌዎቹ በሚታደሱበት ጊዜ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች ፍላጎት መካተቱን ማረጋገጥ

**የቀበሌ ውሀ አቅርቦትና ስነ-ንፅህና ቡድን የንፁህ መጠጥ ውሀና ስነ-ንጽህና አቅርቦት አስፈላጊነት ቅስቀሳና ትምህርት በሚሰጥበት ወቅት የአካል ጉዳተኝነት ጉዳዮችን በአግባቡ በማካተት መቀስቀስ ይጠበቅባቸዋል ቅስቀሳው ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል መድረስ ይኖርበታል**

- የማህበረሰቡን አባላት፣ የወላጅ-መምህራን ህብረት እና የጤና ኮሚቴዎችን የአካል ጉዳተኝነት ግንዛቤ ማሳደግ
- አካል ጉዳተኛ ወይም አረጋውያን ላሉባቸው ቤተሰቦች የውሀ እና መጸዳጃ አገልግሎት መስጫዎቻቸው ተደራሽ ሊሆኑ የሚችሉባቸውን የአሰራር መፍትሔዎች በተመለከተ መረጃ መስጠት
- የአካል ጉዳተኛ ሰዎችን ተሳትፎና አስተዋፅኦ በተመለከተ ማህበረሰቦችን ማማከርና ትግበራውን መከታተል
- በስልጠናዎችና በስብሰባዎች የአካል ጉዳተኛ ሰዎችን ተሳትፎ ማመቻቸትና መከታተል

**የትምህርት ቤቶች አመራርና የልዩ ፍላጐቶች ትምህርት አስተማሪዎች /ባሉበት/ ሚናና ኃላፊነት፡**

- የትምህርት ቤቱን ሠራተኞች፣ የተማሪዎችንና የማህበረሰቡን የአካል ጉዳተኛነት ግንዛቤ ማጎልበት
- በትምህርት ቤቶችና በትምህርት ቤቶች አካባቢ የሚገኙ የአካል ጉዳተኛ ልጆችን በተመለከተ መረጃ ማሰባሰብ
- የአካል ጉዳተኛ ልጆች በትምህርት ቤቶች ክበብ ስልጠና እንዲሳተፉ ማመቻቸትና መከታተል
- በትምህርት ቤቶች የተገነቡ የዋሽ አገልግሎት መስጫዎች አካታች ንድፍን የተከተሉ መሆኑን ማረጋገጥ
- የትምህርት ቤቶች ውሃና መጸዳጃ አገልግሎት መስጫዎች ለሁሉም ተጠቃሚዎች ተስማሚ ይሆኑ ዘንድ በንጹህ ሁኔታ የተያዙ መሆኑን ማረጋገጥ
- የትምህርት ቤቶች የንፅህና አገልግሎት መስጫዎች ለአካል ጉዳተኛ ልጃገረዶች ተደራሽ የሆነ የወር አበባና ንጽህና መስጫ ልዩ ክፍል ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ

**የጤና ጣቢያዎች፣ የጤና ኬላዎች፣ የጤና ኮሚቴ፣ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ የማህበረሰብ ተኮር መልሶ ማቋቋም ሠራተኞች ሚናና ኃላፊነት፡**

- የሴቶች የልማት ቡድን አባላት የአካል ጉዳተኝነትን በዋሽ ስለማካተት ያላቸውን ግንዛቤ ማሳደግ
- የአካል ጉዳተኛ ሰዎች ላሏቸው ቤተሰቦች የአጋዥ መሣሪያዎች እና የውሃ፣ የግል ንጽህና እና የአካባቢ ጤንነት መፍትሔዎች ስለመኖራቸው ምክር መስጠት

- ለቤተሰቦችና ለሴቶች የልማት ቡድን አባላት ያሉትን አካታች የውሃ አቅርቦትና ስነ-ንጽህና ማስተዋወቂያ ቁሳቁሶችን ማሠራጨት
- በጤና ጣቢያዎች ወይም/እና በጤና ኬላዎች በአካባቢው ያሉ የአካል ጉዳተኛ ሰዎችን መረጃ መሰብሰብ
- በጤና ጣቢያዎችና ኬላዎች የተገነቡ የውሃና መጸዳጃ አገልግሎት መስጫዎች አካታች ንድፎችን የተከተሉ መሆኑን ማረጋገጥ
- በጤና ጣቢያዎችና ኬላዎች የተገነቡ የውሃና መጸዳጃ አገልግሎት መስጫዎች ለሁሉም ተጠቃሚ ተስማሚ በሚሆኑበት መልኩ ንፅህናቸው የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ

**የሴቶች የልማት ሠራዊት / ቡድን ሚናና ኃላፊነት፡**

- የአካል ጉዳተኞች ላሏቸው ቤተሰቦች ስለ አጋዥ መሣሪያዎች መኖርና የውሃ፣ የግል እና የአካባቢ ጤና መፍትሔዎች በመኖሪያ ቤት ደረጃ ያሉ ስለመሆኑ ምክር መስጠት
- የውሀና ንጽህና ማስተዋወቂያ ቁሣቁሶች ለመኖሪያ ቤቶች ማሠራጨት
- የአካል ጉዳተኛ ሰዎችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች መስጠት

**የውሃና ስነ-ንጽህና ኮሚቴ፣ የወላጅና መምህራን ህብረት እና የጤና ኮሚቴዎች ሚናና ኃላፊነት፡**

- የአካል ጉዳተኛ ሰዎችን በኮሚቴዎች ውስጥ እንዲመረጡ ማበረታታት
- የአካል ጉዳተኛ ሰዎች ከውሀና ስነ-ንጽህና አገልግሎት መስጫዎች ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ውስጥ የመሳተፍና ውሣኔ የመስጠት እኩል ዕድል እያገኙ መሆኑን ማረጋገጥ
  - ስብሰባዎችን ተደራሽ በሆኑ ቦታዎች ማካሄድ
  - ሁሉም አባላት መጋበዛቸውን ማረጋገጥ
  - ሁሉም አባላት ሃሳባቸውንና ፍላጐታቸውን የሚገልጹበትን ሁኔታ ማመቻቸት
- የተገነቡ የውሀና ስነ-ንጽህና አገልግሎት መስጫዎች አካታች ንድፎችን የተከተሉ መሆኑን ማረጋገጥ
- የውሃ ተቋሙ ያለበት ቦታ ለመድረስ ለማይችሉ የማህበረሰብ አባላት፣ ከአሰራርና ከወጪ አንጻር ተቀባይነት እስካለው ድረስ ሌሎች አማራጮችንም በመጠቀም ውሃ እንዲያገኙ መደረግ አለበት፡፡ /ለምሳሌ፡ ከምንጩ እስከ መኖሪያ ቤቶች የውሃ ቧንቧ በመዘርጋት፣ የጣሪያ ውሃ በማጠራቀም፣ ግቢ ውስጥ የውሃ ጉድጓድ በመቆፈር፣ ውሃን በማከም /በማጣሪያና በኬሚካል/
- የአካል ጉደተኞች ያሉባቸው ቤተሰቦች፣ የአካል ጉዳተኞችንና አረጋውያንን ጨምሮ ለሁሉም ተደራሽ በሆነ መልኩ መፀዳጃ ቤታቸውን እንዲሠሩ ወይም ያላቸውን እንዲያስተካክሉ ማበረታታት

**የዕምነት ተቋማት ሚናና ኃላፊነት፡**

- የማህበረሰቡ አባላት አካል ጉዳተኝነትን እንደ ርግማን፣ ሸክም እና አሳፋሪ ነገር እንዳይመለከቱና አዎንታዊ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ
- ለምእመኖቻቸው በሙሉ የግልና እና የአካባቢ ንፅህናን ጥቅሞችን እንዲረዱ ማድረግ
- ለማህበረሰቡ ምሣሌ የሚሆኑ በዕምነት ቦታዎች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ የሆኑ መፀዳጃ ቤቶችን መገንባት

**ሌሎች ማህበረሰብ ነክ ድርጅቶች / እድር፣ የወጣቶችና ሴቶች ማህበራት ሚናና ኃላፊነት፡**

- አካል ጉዳተኝነትን አስመልክቶ በህብረተሰቡና በማህበራቱ አባላት ውስጥ በጎ ግንዛቤ እንዲሰርጽ ማበረታታት
- በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የውሃና የስነ-ንጽህና አገልግሎት መስጫዎች በሙሉ አካታች እንዲሆኑ በማሻሻል ረገድ አባሎቻቸው እንዲሳተፉ ማንቀሳቀስ

## 8. ስለአካታችነት መዘንጋት የሌለባቸው ነጥቦች

**የመጸዳጃ ቤት/ውሃ ጣብያ መዳረሻ**

መጸዳጃ ቤቱ/ውሃ ጣብያው ከመኖሪያ ቤት/ከተቋም ያልራቀ ነው? (የቤተሰብ መጸዳጃ ከ15 ሜትር ያልበለጠ፣ የድርጅት ከ30 ሜትር ያልበለጠ) መሆን

ወደ መጸዳጃ ቤት/ውሃ ጣብያ የሚወስወደው መንገድ ሰፋ ያለ፣ ጠበቅ ተደርጎ የተደለደለ፣ የማያሳስትና የማያደናቅፍ ነው?

መንገዱ እንዳያሳስት ግልጽ ምልክቶች ተደርገውበታል? (ለምሳሌ በድንጋይ፣ በገመድ፣ በቀለም)

**የመጸዳጃ ቤት/ውሃ ጣብያ ተደራሽነት**

ለአጠቃቀም ቀላልና አደጋ የማያስከትል ነው? (የተጋነነ የደረጃ ከፍታ ያለመኖር፣ የእጅ መደገፊያዎች በቦታቸው መኖር፣ የሽንት ቤቱ ቀዳዳ ያለበትን ቦታ የሚያመለክቱ ተዳሳሽ ምልክቶች መኖር)

ራምፕና(መወጣጫ) ሌሎች የመወጣጫ የእጅ መደገፊያዎች ወይም አመቺ መሸጋገሪያ አለው? የራምፑ ተዳፋትነት ልከኛ ነው? (በ1 ሜትር ርዝመት ውስጥ ከ10 ሳሜ ያልበለጠ ከፍታ)

የመጸዳጃ ቤቱ መግቢያ በር በቂ ስፋት አለው? (ቢያንስ 90 ሳሜ)

የመጸዳጃ ቤቱ መዝጊያ በቀላሉ የሚከፈትና የሚዘጋ ነው? በሩ ከውጭና ከውስጥ በኩል እጀታዎች አሉት?

የውሃ ተቋሙ አጥር በራምፑ ተጠቅሞ የውሃ መቅጃውጋ ለመድረስ መሰናክል አይሆንም?

**ለአጠቃቀም አመቺነት**

መጸዳጃ ቤቱ ተጠቃሚዎችን ከእይታ መከለል የሚችል ነውን?

መጸዳጃ ቤቱ/የውሃ ጣብያው በውስጡ አካል ጉዳተኛ እንደልብ ተዘዋውሮ ለመጠቀም የሚያስችል በቂ ስፋት አለው?

መጸዳጃ ቤቱ የተለያየ አይነት የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች የሚሆኑ አማራጭ መቀመጫዎች አሉት?

መጸዳጃ ቤቱ የመደገፊያ ዘንጎች ተገጥመውለታል?

የመጸዳጃ ቤቱ/የውሃ ጣብያው ወለል የተሰራው ከማያዳልጡና በቀላሉ ሊጸዱ ከሚችሉ ቁሳቁሶች ነው?

በውሃ ምንጮች ላይ የተገጠሙት የቧንቧ መክፈቻዎች የተለያዩ ከፍታዎች እንዲኖሯቸው ተደርጓል?

**ማህበራዊ አካታችነት**

ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት፣ አካል ጉዳት ያለባቸውን ጨምሮ፣ በውሃና ስነ-ንጽህና ጉዳዮች ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ተጋብዘዋል?

ስብሰባዎቹ በተቻለ መጠን ለሁሉም የህብረተሰቡ አባላት አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ አመቺ በሆነ ቦታ ላይ እንዲካሄዱ ተደርጓል?

የአካል ጉዳተኛ ሰዎች በዋሽ እቅድ አዘገጃጀት፣ አስተዳደር እንዲሁም አገልግሎት አሰጣጥና ጥገና እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተሳታፊ ሆነዋል?

በውሃና ንጽህና ኮሚቴዎች ውስጥ አካል ጉዳተኛ ሰዎች ተካትተዋል?

በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች ተለይተው ታውቀዋል? ፍላጎታቸውስ በውሃና ስነ-ንጽህና ፕሮጀክት እቅድና ትግበራ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል?

አካል ጉዳተኛ ሰዎች ያሉባቸው ቤተሰቦች መጸዳጃ ቤቶቻቸውን ተደራሽ ሊያደርጉ ስለሚችሉበት መንገድ ምክር አግኝተዋል?

አካል ጉዳተኛ ሰዎች ከሌሎች እኩል ከፕሮጀክቱ ተጠቃሚ መሆንና አስተዋጽኦ ማድረግ ችለዋል?

የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ወይም ቡድኖች (ባካባቢው ካሉ) እንዲሳተፉ ወይም አስተያየት እንዲሰጡ ተደርጓል?